<u>የፀረ ወያኔ ትግላችንን የሚመራው ወያኔ ራሱ ይሆን?</u>

ዕጌረዳ ተሰማ

የመረጥኩት ርዕስ  አስገራሚ ሊመስል ይችላል ግን ባለፉት ዓመታት የተከሰተውን ሁሉ ሳይ ፀረ ወያኔ ፀረ ኢሕአዴግ የምንለውን ትግል ራሱ መለስ ዜናዊ ወይም ወያኔ እየመራው  ይመስላል። ይህን ለምን አልኩ?

1ኛ/ በወያኔ ሰርጎ ገቦችና ቅጥረኞች ዋና ስራ የተነሳ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ተከፋፍለዋል፤
2ኛ/ ወያኔ በየጊዜው የቤት ስራ እየሰጠ በዚያው ስንደፋደፍ ዋናውን ተልዕኮ ሊያስተን ሊያስረሳን ችሏል።

በቅርቡ እንጀምር። የህብረት ጥረት ፍሬያማ ሊሆን በቻለበት ወቅት ቅጥረኛውን ልደቱ አያሌውን አንቀሳቅሶ በታወጀበት ቀን ጀምሮ ችግር ፈጠረበት። በቀጥተኛና እጅ አዙር ቅጥረኞቹ አማካይነት ይህን ህብረት ሊያደናቅፍም ቻለ ። በዚሁ ተልዕኮ  ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፣ ልደቱ አያሌው፣ ፕሮፌሰር መስፍንና ክፍሉ ታደሰ የነበራቸው አሉታዊ ሚና የሚታወቅ ነው። ቅንጅት ተመሰረተ ። ይህንንም ስብስብ ለማዳከም እነ ልደቱ ተሰማሩ። በ1997 ምርጫ ቅንጅትና ህብረት ያልተጠበቀ ውጤትን ሲያመጡ አፈናው ተካሄደ። ከዚሁ አፈና ጋር ደግሞ ድርጅቶችን ለመከፋፈል በየአቅጣጫው በመሰማራት በአንድ በኩል በህብረት ውስጥ ያሉትን በጥቅምና በማስፈራራት ሲያስገብር በሌላ በኩል ደግሞ ልደቱና ሌሎችን ተጠቅሞ ቅንጅትንም ከፈለው። የተከተለውን ሁላችን እናውቃለን። ቅንጅትንም መሪዎቹ ከቃሊቲ ከወጣ በኋላ እንደገና ከፈሉት።የብረሃኑና ብርቱካን ሚና በዚሁ ይጠቀሳል። ከዚሁ ጋር ለወያኔ በጠላትነት የተሰለፈውን ኢሕአፓንም ሰርገው የገቡ የወያኔና የባዕድ ሀገር ቅጥረኞች ከፋፈሉት። በዚህ ድርጅት ረጅም ትግል የተሰላቹና ዕድሜያቸው የገፋ ተስፋ በመቁረጣቸው ለእነዚህ ሰርጎ ገቦች ሰለባ ሆኑላቸውና በኢሕአፓም ክፍፍል ወይም አንጃነት ዳግም ተከሰተ። ከየድርጅቱ የወጡት አንጃዎችና አፍቅሮ ወያኔ ያላቸው ሀይሎች ዛሬ ተቀናጅተው ወይም ሊተባበሩ ሲፍጨረጨሩ ስናይ ሴራው የወያኔ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን። ወያኔ ተቃዋሚ ሀይሎችን መከፋፈል ስራው ስለሆነ በእሱ ማማረር ሳይሆን ተቃዋሚ ሀይሎች ራሳቸውን

መጠበቅ ነው ያለባቸው።

ወያኔ ትግላችንን እየመራ ይሆን ብሎ የሚያስጠይቀው ሌሌ ክስተት በየጊዜው ወያኔ የምንጮህበት አጀንዳ እየሰጠ በዋና ጥያቄዎች ላይ እንዳናተኩር ማድረጉ ነው። በ1997 የሕዝብን ድምፅ ካፈነ በኋላ የሕዝብ ድምፅ ይከበር የሚለውን ዋና መፈክር በእስረኞቻችን ይፈቱ እንዲተካ አደረገ ። ባለ ስምንት ነጥብ ጥያቄ አለን ብለው መሰረታዊውን ወያኔ ህገወጥ ነውና ይውረደንም እንዲዘነጉ አደረገ ። የታሰ ሩት እስረኞቻችን ይፈቱ ያሉት ያውም የኢሠፓው የቀድሞ ኢንጂነር ግዛቸው እንደገለጠው ሀሉንም እስረኛ ሳይሆን “ የእኛን ብቻ” የሚል ሆኖ ወያኔ የሕዝብ ድምፅ ሰርቋልና ህገወጥ ነው ይውረድ በሚል ዙሪያ ትግል ሊካሄድ አልቻለም። ወያኔ እስራትን ለብዙ ውጤት ይጠቀምበታል። የራሱን ቅጥረኞች አስሮ በማንነታ ቸው ላይ ለማዳናገር--የልደቱን በዝዋይ ለወር መታሰር ያጤኗል። ወይም ከዋናው የትግል ትኩረት የሕዝብን ትኩረት ለመቀየር። በዚህም በዚያም ግን በሚፈልገው ይቃኘናል ማለት ነው። የነመለስ አገዛዝ በህገወጥ ስልጣን ተፈናጦ እያለ፣ ሶማሊያን ወሮ ዜጎችን አስጨርሶ፣ በኦጋዴን ጭፍጨፋ አካሂዶ፣ የሀገርን መሬት ለሱዳን ሰጥቶ ፣ሀገርን በዝብዞ ሕዝብን ለረሀብና መከራ አጋልጦ እያለ፣ ከ35 ሺ ዜጋ በላይ በእስር እያማቀቀ እያለ ይህን በመቃወም ዓለም አቀፍ ሰልፍ እናድርግ የሚል ምንም ጥሪ ሳይሰማ ዛሬ ብርቱካን ሚዲቅሳ ተያዘች በሚል ሰልፍ ይደረግ በሚል ኡኡ እንድንል አድርጎናል።

ትላንት ልደቱና ማንዴላ ይል የነበረ አንድ ግንዛቤ ያጠረው ግለሰብ ዛሬ ብርቱካን የበርማዋ አንግ ሱን ኪ ዓይነት የሰላም አርበኛ ናት ይለናል። በሀገራችን ሴት አርበ ኞች ጠፉ? ከብርቱካን በፊት በፖለቲካ ድርጅቶች ዋና ሚና ተጫውተው መታሰር ሳይሆን መስዋዕት የሆኑ ጠፉ? የበርማዋ ትግልና ከወያኔ ጋር በምርጫ ልትተቃቀፍ የወሰነችው ብርቱካን ምን ይመሳሰላል? ብርቱካን ትላንት ከመቶ የፖለቲካ እስረኛ በላይ የለም ስትለን አልነበረም? የተያዘችው አንዳንዶች እንደሚሉት እንደ ልደቱ ለይስሙላ ቢሆንም እንኳን ብርቱካን ትፈታ ብሎ መጠየቅና መጮህም ይገባል። ወያኔ ዝና ሰጥቶ በመጪው ምርጫ ሊያሰልፋትና ለራሱ ትርፍ ሊያገኝ ቢሆን ቢች ልም በህገወጥ መንገድ ስለታሰረች ትፈታ ማለቱ ተገቢ ነው። እሷም፣ቴዲ አፍሮም ፣ በተለይም ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ብሎ መጮህ ያስፈልጋል። ግን ይህ

ዋና አይደለም፤ ይህ ብቻ አይደለም የትግል መፈክራችን መሆን ያለበት። ወያኔ ይውረድ ብለን መታገል መቻል አለብን። ወያኔ እያወጣ ባላቸው ህገወጥ ድንጋጌዎች ላይ ማተኮር አለብን። ወያኔ በየቦታው በሚፈፅመው ፍጅት ላይ ማተኮር አለብን። በመጪው ምርጫ ማንም ሀይል እንዳይሳተፍ መጣር አለብን። ወዘተ ወዘተ የራሳችንን የትግል አጀንዳና ግብ ይዘን መታገል አለብን እንጂ ወያኔ የትግላችንን ይዘትና ትኩረት ሊቃኝልን ሊወስንልን አይገባም። በወሳኞቹ ጉዳዮች ላይ እያንቀላፋን ወያኔ በሚቀሰቅሰን መለስተኛ ጥያቄዎች ላይ ማተኮር የለብንም። የወያኔን ሴራ አውቀውም ሆነቅ ሳያውቁ እያጀቡ ትግላችንንም የሚጎዱት ግለሰቦችም ከዚሁ ድርጊታቸው መቆጠብ አለባቸው። ለፖለቲካ እስረኞች በሞላ መፈታት--ለአንድ ወይ ሁለቱ ብቻ ሳይሆን-የምናደርገው ትግል ተገቢ ሲሆን ወያኔ ይወገድ ብለን በዋናው መሰረታዊ ጉዳይ ላይ አተኩረን ማካሄድ ያለብንን ትግል ሊቀድም ሆነ ሊሸፍን አይችልም ወይም አይገባውም።

ወያኔ ትግላችንን አይቀማን!!!